ቀን Date, ሕዳር 03 2017
ቁጥር Ref.No ገ.ሰ/ገ40/17

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ
ባሉበት

ጉዳዩ፦ <u>የጸደቀ መመሪያ መላክን ይመለከታል፤</u>

በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 19(4)መሰረት የታክስ ደረሰኝ አጠቃቀም እና አስተዳደር መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 188/2017 ለቀጣይ አፈጻጸም እንዲያመች 8 ገጽ አባሪ ተያይዞ ተልኳል።

ከሠላምታ ጋር

ፍቃዱ ታደሰ ገ/ሚካኤል
የሚኒስትር ጽ/ቤት ኃላፊ

<u>ግልባጭ፤</u>

- ለሚኒስቴር ጽ/ቤት
- ለታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለታክስ ስርዓት ዘርፍ
- ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ቢሮ

<u>ገቢዎች ሚኒስቴር</u>

<u>አባሪዎች፦</u>

- **ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት**
- **ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር 1 ቅ/ጽ/ቤት**
- **ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር 2 ቅ/ጽ/ቤት**
- **ለምስራቅ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት**
- **ለምዕራብ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት**
- **ለሰሜን ምዕራብ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት**

<u>አዲስ አበባ</u>

- **ለአዳማ ቅ/ጽ/ቤት**

<u>አዳማ</u>

- **ለሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት**

<u>ሀዋሳ</u>

- **ለድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት**

<u>ድሬዳዋ</u>

- **ለጅማ ቅ/ጽ/ቤት**

<u>ጅማ</u>

- **ለባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት**

<u>ባህር ዳር</u>

- **ለመቐለ ቅ/ጽ/ቤት**

<u>መቐለ</u>

- **ለኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት**

<u>ኮምቦልቻ</u>

መመሪያ ቁጥር 188/2017

የታክስ ደረሰኝ አጠቃቀም እና አስተዳደር መመሪያን ለማሻሻል የወጣ /ማሻሻያ/ መመሪያ

አዲስ አበባ፤

ጥቅምት 2017 ዓ.ም



መመሪያ ቁጥር 188/2017

የታክስ ደረሰኝ አጠቃቀም እና አስተዳደር መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

ለእያንዳንዱ የንግድ ሥራ ዘርፍ እና የንግድ አድራሻ የተለያየ ደረሰኝ እንዲታተም ማድረግ አስፈላጊ ስለሆነ እና በእያንዳንዱ ደረሰኝ ላይ ልዩ መለያ QR ኮድ (unique QR code) ማካተት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ገቢዎች ሚኒስቴር በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 19(4) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን የማሻሻያ መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. አጭር ርዕስ

   ይህ መመሪያ "የታክስ ደረሰኝ አጠቃቀም እና አስተዳደር መመሪያ /ማሻሻያ/ ቁጥር 188/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ማሻሻያ

   የታክስ ደረሰኝ አጠቃቀም እና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 149/2011 (በፍትህ ሚኒስቴር ቁጥር 165/2013) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

   1/ በመመሪያው አንቀጽ 4 ላይ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 ተካቷል፡፡

   "3/ እያንዳንዱ የደረሰኝ ቅጠል ሲታተም ልዩ መለያ ኮድ (unique QR code) ተካቶ ካልታተም ተቀባይነት አይኖረውም፡፡"

   2/ በመመሪያው አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ ከፊደል "ቸ" ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ፊደል "ኘ" ተጨምሯል፡፡

   "ኘ) ማንኛውም አታሚ ደረሰኝ ሲያትም በታክስ ባለስልጣኑ የተዘጋጀውን ልዩ መለያ ኮድ (unique QR code) በመውሰድ በእያንዳንዱ የደረሰኝ ቅጠል ላይ አካቶ ሊያትም የሚገባው ሲሆን፤ ሲያትም የልዩ መለያ ኮዱ ወርድና ቁመት ቢያንስ 2 ሴንቲ ሜትር ሆኖ በደረሰኙ የቀኝ ራስጌ ላይ መታተም አለበት፡፡"

   3/ የመመሪያው አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (4) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (4) ተተክቷል፤

   "4/ ከአንድ በላይ የንግድ ሥራ ዘርፍ እና የንግድ አድራሻ ያለው ታክስ ከፋይ፤

   ሀ) ድርጅት ከሆነ፡-

   (1) የማንዋል ደረሰኝ ለማሳተም ጥያቄ ሲያቀርብ ለእያንዳንዱ ቅርንጫፍ የሚያስፈልገውን የጥራዝ ብዛት መግለጽ አለበት፤

ከበረ አበበ መንግሻ
የሚኒስትር ሕግ አማካሪ

(2) ከዋናው አድራሻ በተጨማሪ ደረሰኙ ሊታተምለት የተፈለገው የንግድ ዘርፍ እና የቅርንጫፍ አድራሻው ተገልጾ መታተም አለበት፡፡

ለ) ግለሰብ ከሆነ፡-

(1) የማንዋል ደረሰኝ ለማሳተም ጥያቄ ሲያቀርብ እያንዳንዱ የንግድ ሥራ ዘርፍ ለሚካሄድበት ቦታ የሚያስፈልገውን የጥራዝ ብዛት መግለጽ አለበት፤

(2) ከዋናው አድራሻ በተጨማሪ ደረሰኙ ሊታተምለት የተፈለገው የንግድ ዘርፍ እና የንግድ ሥራ ዘርፉ የሚካሄድበት ቦታ ወይም አድራሻ ተገልጾ መታተም አለበት፡፡"

4/ በመመሪያው አንቀጽ 24 ላይ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች ተካተዋል፡፡

"9/ ማተሚያ ቤቱ በማንዋል ደረሰኝ QR-code አስተዳደር ፖርታል (Manual Receipt QR-code Web Portal) የተጋራውን መረጃ (ዳታ) ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ በማድረግ ደህንነቱን እና ሚስጥራዊነቱን የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

10/ ማተሚያ ቤቱ ምንም አይነት ስህተት ወይም ልዩነት ሳይኖር ደረሰኞችን ልዩ መለያ ኮድ (unique QR code) በማካተት ለማተም በማንዋል ደረሰኝ QR-code አስተዳደር ፖርታል (Manual Receipt QR-code Web Portal) የተጋራውን ዳታ በትክክል ተቀብሎ የመተግበር ግዴታ አለበት፡፡

11/ ማተሚያ ቤቱ በማንዋል ደረሰኝ QR-code አስተዳደር ፖርታል (Manual Receipt QR-code Web Portal) በኩል ዳታ ሲጋራ ተገቢነት ያላቸውን ሁሉንም የዳታ ጥበቃ ደንቦችና መመሪያዎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

12/ ማንኛውም ማተሚያ ቤት ልዩ መለያ ኮድ ያለው ማንዋል ደረሰኝ ሲያትም በወረቀቱ ላይ ሊሰርግ የሚችል ኢንክ ጀት (Ink jet) የሚባል ቀለም የመጠቀም ግዴታ አለበት፡፡

13/ ማንኛውም ማተሚያ ቤት እንዲታተም የተፈቀደውን እና የታተመውን ደረሰኝ በተመለከተ በተዘጋጀው ሲስተም በወቅቱ ሪፖርት የመላክ ኃላፊነት አለበት፡፡

14/ ማንኛውም ማተሚያ ቤት በታክስ ከፋዩ ደረሰኝ እንዲያትም ሲጠየቅ፤ በታክስ ባለስልጣኑ ለታክስ ከፋዩ የተሰጠ የደረሰኝ ህትመት ፈቃድ ደብዳቤ ሳይቀበል ደረሰኝ ማተም የለበትም፡፡

አበረ አበበ መንገሻ
የማኒስትር ሕግ አማካሪ

15/ በዚህ መመሪያ መሰረት የደረሰኝ ህትመት አገልግሎት የሚሰጥ ማተሚያ ቤት ከሚኒስቴሩ ጋር የቅንጅት አሰራር ስምምነት የማድረግ ኃላፊነት አለበት።"

3. <u>መሸጋገሪያ</u>

1/ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ይህ የማሻሻያ መመሪያ ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት አሳትሞ ያልተጠቀመባቸው ደረሰኞች መጠቀም የሚችለው የማሻሻያ መመሪያው ተፈጻሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ባለው ለሶስት ወር ጊዜ ብቻ ነው።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋሉ ደረሰኞችን በተመለከተ ታክስ ከፋዩ ተመዝጋቢ ለሆነበት የታክስ ባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት ሪፖርት በማድረግ ደረሰኞቹ እንዲወገዱ የማድረግ ግዴታ አለበት።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀው ቢኖርም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (3) የተገለፀው ይህ መመሪያ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በሚታተሙ ደረሰኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

4. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበበት እና በገቢዎች ሚኒስቴር ድህረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ፣ ጥቅምት 2017 ዓ.ም

ኢዮብ ሳሙኤል አሰፋ
ሚኒስትር

የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር

ከሰረ ኦሰመ መንገሸ
የሚኒስትር ሕግ አማካሪ

Directive No. 188/2024

Tax Invoices Usage and Administration /Amendment/

Addis Ababa;

October 2024

Abere Abebe Mengesha
Legal Advisor of the Minist

Directive No. 188/2024

A Directive to amend Tax Invoices Usage and Administration Directive

WHEREAS, it has become necessary to make a taxpayer use different invoices for each of the businesses categories and each of his business places, and it has become essential to include a unique QR code on each tax invoice;

NOW, THEREFORE, the Ministry of Revenue with the power vested in it in accordance with Article 19(4) of the Tax Administration Proclamation No. 983/2016 has issued this amendment Directive as follows:

1. **Short Title**

   This Directive may be cited as "Tax Invoices Usage and Administration /Amendment/ Directive No. 188/2024".

2. **Amendment**

   Tax Invoices Use and Administration Directive No. 149/2019 (No. 165/2021 in the Ministry of Justice) is hereby amended as follows:

   1/ The following new sub-article 3 is added under Article 4:

   "3/ Each tax invoice must include a unique QR code when printed; otherwise, it shall not be acceptable."

   2/ The following new sub-article "m" is added to sub-article (l) under article 6 sub-article (1).

   "m/ When any printing enterprise prints a tax invoice, it is a must to take the unique QR code prepared by the tax authority and include it on each invoice sheet. This unique QR code should be printed on the right header of the invoice with a width and height not less than 2 cm."

   3/ Sub-article (4) of Article 7 is repealed and replaced by the following new sub-article (4).

   "4/ If a taxpayer with more than one line of business activity and business addresses:

   a/ is a company:-

Abere Abebe Mengesha
Legal Advisor of the Minister

(1) it must specify the number of volumes required for each branch; when requesting a permit to print manual invoices,

(2) in addition to the main address, the line of business for which the invoice is to be printed and the branch address must be specified on the invoice.

b/ is an individual:-

(1) it must specify the number of volumes required for each branch; when requesting a permit to print manual invoices,;

(2) In addition to the main address, the line of business for which the invoice is to be printed and the branch address must be specified on the invoice.

4/ The following new sub-articles have been added to Article 24 of the Directive.

"9/ Any printing press enterprise has a duty to protect the security and confidentiality of the data shared by the Manual Receipt QR-code Web Portal by not transferring it to third parties.

10/ Any printing press enterprise has a duty to accept and implement the data shared by the Manual Receipt QR-code Web Portal to print invoices with appropriate QR code without any errors or discrepancies.

11/ Any printing press enterprise has a duty to comply with all applicable data protection rules and regulations when sharing data through the Manual Receipt QR-code Web Portal.

12/ Any printing press enterprise has a duty to use an ink jet ink that can penetrate or pass through the paper when a manual receipt is printed with a QR code.

13/ Any printing press enterprise has a duty to send a timely report about the invoices permitted to be printed and printed invoices through the system prepared for this purpose.

14/ Any printing press enterprise shall not print tax invoices for any taxpayer without receiving a letter of permission from the tax authority.

15/ Any printing press enterprise that provides invoice printing services in accordance with this Directive has a duty to make a coordination agreement with the ministry. "

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues

Abere Abebe Mengesha
Legal Advisor of the Minister

3. **Transitional Provisions**

1/ Any taxpayer who printed tax invoices before the coming into force of this Amended Directive and has not used them yet can use them only within three months from the effective date of this Directive. .

2/ The invoices not used within the period given under sub-article (1) of this Article shall be reported to the relevant tax authority and be disposed of.

3/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the provisions of sub-article (3) of Article 2 of this Directive shall apply to invoices printed after the effective date of this directive.

4. **Effective Date**

This Directive shall be effective from the date of its registration by the Ministry of Justice and its uploading on the website of the Ministry of Revenue.

Addis Ababa; October 2024

Aynalem Nigusie Ali

Minister of the Revenues Ministry

Abere Abebe Mengesha
Legal Advisor of the Minister